# ልጅ ሄኖክ የሽጥላ፡- ባለጌና ዋንጫ ከወደ አፉ ሰፊ ነው

**መለከ ሐራ ከቤተ አማራ (Melek Hara)፣ August 19 at 9:46pm**

**ምንጭ፡-** https://www.facebook.com/permalink.php?story_fbid=151374988531945&id=100009783333517&fref=nf

==============================

በቅድሚያ የአማራን ክብር አናስደፍርም ለምትሉ እና የቤተ አማራ ወዳጅ እና ደጋፊ አማሮች ይህን ማለት ወደድሁ፡፡ እኛ ማንንም ግለሰብም ሆነ አካል ተንኩሰን አናውቅም፡፡ ብዙ ጊዜ እየመጡ የሚተነኩሱንም እነሱ ናቸው፡፡ ዝም የምንላቸውም መልስ ብንሰጣቸው እኛው ራሳችን "ወያኔ ናቸው" የሚል ስም ስለሚለጠፍብን እና እናንተም ግርታ ውስጥ እንዳትወድቁ በማሰብ ነው፡፡ ዛሬ እኔ በግሌ አባቶቻችንን እና ጠቅላላ ህዝባችንን ለተሳደበው ልጅ ሄኖክ መልስ መስጠት እወዳለሁ፡፡ ምክንያም እዚህ የተቀመጥኩት ወገኔ ሲሰደብ እና ሲዘለፍ ዝም ብየ ለማየት ስላልሆነ፡፡ አማራን የሚነካ እንኳን አንድ ጥራዝ ነጠቅ ጎረምሳ ይቅርና ፈጣሪንም ቢሆን እሟገተዋለሁ፡፡ ወደመሀል ልግባ፡-

አማራን መስደብ ሽልማት ያስገኛል፡፡ ልጅ ሄኖክም የታሰበለትን ሽልማት ለማግኘት ይመስላል አማራን በጠቅላላው የዘለፈው፡፡ ለምን ቢባል ይህንን አማራን የሚሰድብበትን ጽሁፍ ላይክ ካደረጉት ሰዎች አማርኛ ተናጋሪ የኢሳት ጋዜጠኞች ይገኙበታል፡፡ አማራ መሰደቡ ደስ ብሏቸው ማለት ነው፡፡ ልጅ ሄኖክ አማራን ሰድቦ ገጸ በረከት ሲያቀርብ እየተጨበጨበለት መሆኑ ነው፡፡ እንዴው ነገሩ ነው እንጅ ኧረ ይመቻችሁ፡፡ ግን አማራን የሰደበ የሚሾም ወያኔ ብቻ ሳይሆን ሌላም አካል እንዳለ መጠርጠራችንን ሹክ እያልናችሁ፡፡

መጀመሪያ በለጠፍከው (ሰው ሲተችህ ከማስተካከልህ በፊት የነበረው) ጽሁፍህ ውስጥ "ያማራ ልሂቃን፣ ዋነኛ ጠላታቸው አስተሳሰባቸው እንደሆነ ዛሬም ድረስ የተረዱት አይመስለኝም" ብለሀል። ይህንን አረፍተ ነገር ዝም ብሎ ማስቀመጥ ከስነጽሁፍ ህግም ከአመክንዮም አንጻር አያስኬድም፡፡ መነሻም መድረሻም ሳኖረው እንዲሁ በድምዳሜ መልክ የተቀመጠ ነው፡፡ የትኛው አስተሳሰባቸው እንደሆነ ጠላታቸው አልተገለጸም፡፡ እንግዲህ አስተሳሰቦች እጅግ ብዙ ናቸውና ከነዛ አስተሳሰቦች ውስጥ የቱ ወይም የትኛው አስተሳሰብ የአማራ ልሂቃን ጠላት እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ ያ ጠላታቸው ከምን አንጻር ጠለት እንድተባለም አልተጠቀሰም፡፡ በመሆኑም ጽሁፍህ መናኛና ረጋ ሰራሽ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ቀጥለህም የአማራ ልሂቃን "በተግባር የተጨበጠ ለውጥ ከማምጣት፣ አሉባልታ ላይ ሙጥኝ ስለማለቱ እንደማሳያ ነው" አልክ፡፡ ይሄውልህ፡- ሲጀመር ሁሉም ልሂቅ ተጨባጭ ለውጥ አያመጣም፡፡ ተጨባጭ ለውጥ የሚባለው ምንነቱ ራሱ የተለያየና አነጋጋሪ ነው፡፡ አላመጡም ብሎ መደምደሙ ራሱ በጣም ችግር ያለበት ጥራዝ ነጠቅ ንግግር ነው፡፡ እዚህ ድምዳሜ ለመድረስ የተወሰነ ጥናት ያስፈልጋል፡፡ ያለምንም ጥናት ወይም ዳሰሳ የሚደረግ ንግግር "መሰለኝና ደሳለኝ" ይባላል፡፡ ስለዚህ የአማራ ልሂቃንን በመሰለኝና ደሳለኝ ልታብጠለጥል አትችልም፡፡

በጣም የሚያሳፍረውና የዘቀጠ ዘረኝነትህን ወይም ወፈፌነትህን የሚያመለክተው ደግሞ "የአማራ ልሂቃን፣ ብርሃኑ ነጋን የሚጠሉበት ዋነኛ ምክንያታቸው፣ ቆሻሻቸውን ስላሳያቸውም ይመስለኛል" ያልከው ዋልጌ ዘለፋ ነው፡፡ አንደኛ ብርሀኑ ነጋን የአማራ ልሂቃን እንደሚጠሉ ከምን ተነስተህ እንደደመደምክ የገለጽከው ነገር የለህም፡፡ ሁሉም ልሁቃን ይጥሉት፤

የተወሰኑት ይጥሉት፤ ከአነ አካቴውም ይጥሉት አይጥሉት ወዘተ ያቀረብከው ነገር የለም፡፡ ዝም ብለህ ከመሬት ተነስተህ ይጠሉታል ልትል አትችልም፡፡ እጠላዋለሁ ያሉህን እንኳ ለመረጃ ያክል ምንጭ ማቅረብ ነበረብህ ይህንን ያክል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ፡፡ ሲቀጥል ብርሀኑ ንጹህ ሌላው የአማራ ልሂቅ ቆሻሻ ነው ማለት የውርጋጥ ድፍረት በስነምግባር የታነጸ ሰው ንግግር አይደለም፡፡ ዶክተር ብርሀኑን ለማመስገን የአማራ ልሂቃንን በጠቅላላ ቆሻሻ ያለባቸው ብሎ መናገር አስፈላጊ አልነበረም፡፡ ቆሻሻነታቸውን ራሱ በምን ለክተህ እንዲህ ደፍረህ ልትናገር እንደቻልክ እግዜሩ ነው የሚያውቀው፡፡ አንተ የምትወደውን ሰው ያልተከተለ ሁሉ ቆሻሻ ነው ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ ግን የሄኖክ አእምሮ ሄኖክ ውስጥ ሞቶ ይታየኛል፡፡ ስለዚህች ንጹህ እና ቆሻሻ የምትል ጠብደላዊ ንግግርህ መቸም በይፋ በአደባባይ ይቅርታ ትጠይቃለህ ብየ አስባለሁ፡፡

የአማራ ልሂቃን ቆሻሻ መሆናቸውን በማወጅ ብቻ አላቆምክም፡፡ የተከበረው ታሪካችን እና የታሪኩ ባለቤቶች ላይ ምላስህን አውጥተህ ዘለፍክ እጅ፡፡ እንዲህም አልክ የአማራ ልሂቃን “በገበየሁ ታሪክ ማኪያቶ ሲጠጡ የኖሩ፣ በገብርዬ ጀግንነት ዘር ሲቆጥሩ የኖሩት፣ በበላይ ሲፎክሩ የኖሩት፣ እነሱ ግን አንዳቸውንም መሆን የማይችሉ እንደሆኑ፣ በይበልጥም ደካሞች እና አቅመ ቢሶች እንደሆነ፣ ፍንትው አርጎ ስላሳያቸው ብርሃኑ ነጋን ይጠሉታል። ጀግንነት ዘር ቆጠራ ሳይሆን መስእዋትነት እንደሆነ ስላሳያቸው፣ አምርረው ይጠሉታል።” ሙጫ ሄኖክ እንዴው እንዲህ ተብሎ ይጻፋል! ማኪያቶ ለመጠጣት የገበየሁ ታሪክ አያስፈልግም፡፡ ማኪያቶም ጠጡ ጉሽ ጠላ የገበየሁ ታሪክ የሚነገረው ታሪክ ስለሆነ እና ታሪክ ደግሞ በራሱ መንገድ የሚነገር ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ በግብርየ ጀግንነት ዘር የሚቆጥሩ ያልካቸው ደግሞ ዘር ቆጥረው ምን እንዳደረጉ፤ ችግሩ ምን እንደሆነ፤ ከዶክተር ብርሀኑ ጋር ምን እድሚያገናኘው አልጠቀስክም፡፡ ገብርየን መጥቀስ የአንድ የተወሰነ ችግር ነው መንስኤ ነው ብሎ የሚያምን አእምሮ ህክምና የሚስፈልገው ነው፡፡ የማይያያዝን ነገር ማገናኘት በተጠየቃዊ ጽሁፍ ውስጥ ተቀባይነት ስለሌለው ድምዳሜህ ጠብደላዊ ሆኖልህ አረፈው፡፡ በበላይ መፎከር ብርሀኑን ለመጥላት ምክንያት ነው ብሎ ማመንም እንዲሁ አሳፋሪ ነው፡፡ እንዳንተ አባባል ብርሀኑን የሚጠሉት እነዚህን ጀግኖች መሆን ስላልቻሉ ነው፡፡ ምን አይነት አስተሳሰብ ነው በወይብላይቱ ማርያም! አበስኩ ገበርኩ! ደግሞም እኮ ጣላት ማድረግ ብቻ ሳይን “ፍንትው” አድርጎ ነው ያሳያቸው፡፡ እንዳንተ አባባል እንግዲህ የአማራ ልሂቃን ጀግንነት በዘር ቆጠራ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ማለትም የአማራ ልሂቃን በሞላ ሙታን ናቸው ማለት ነው፡፡ ሁሉም የአማራ ልሂቅ በዚሁ ባንተ ቀዳዳ ስልቻ ነው የሚቋጠረው ማለት ነው፡፡ ጅል ባያፍር የጅል ዘመድ ያፍር እንድንል አደረግከን እኮ፡፡ የእኛ “አዋቂ” የዚህ ጽሁፍ ግልባጭ ትርጉም ብርሀኑ የጀግና ዘር አይደለም፤ ከራሱ ዘር ውስጥ የመጀመሪያ ጀግና ለመሆን እየተውተረተረ ያለ ነው ማለት ነው፡፡ አሳፋሪ፡፡ ባታውቀው እንጅ ብርሀኑም ለተረት የሚሆኑ ጀግና ቅድመ አያቶች እና ወንድሞች ያሉት መሆኑ ነው፡፡ የቅርቡ ታሪክ ብርጋዴር ጀኔራል ተስፋየ ሀብተ ማርያም የብርሀኑ ነገድ አባል ነው፡፡ ፊታውራ ሀብተጊዮርጊስ ለብርሀኑ ተረት መሆን የሚችል ሰው መሰለኝ፡፡ ራቅ ሲልም ብርሀኑ የመጣው እነሲዲ መሀመድን የመሳሰሉ ጀግኖች ከበቀሉበት አካባቢ መሰለኝ፡፡ አወደስኩ ብለህ ልብሱን ገፍፈህ እርቃኑን አቆምከው እኮ፡፡ የክርክርህ ማሰሪያም ብርሀኑ ከአሉባልታ ወጥቶ መስዋእትነት ከፍሎ አሳቸው የሚለው ነው፡፡ ተው እንጅ፡፡ እስኪ የመስዋእትን ትርጉም አትናው መጀመሪያ፡፡ ሳይሞት፤ ሳይቆስል ታሚርትበታለህሳ ወዳጀ! መስዋእት የሚባለውስ ምን ተጨባጭ ለውት አመጣ ብለህ መመርመር ነበረብህ፡፡ እታች ክፍል ፊዚክስ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ትዝ ካለህ አንድን ግድግዳ ብትገፋው ብትገፋው እስካልጣልከው ድረስ ስራ ሰራህ ማለት አይቻልም የተማርን ይመስለኛል፡፡ ግድግዳውን በመግፋትማ እንግዲያው አንተ አሉባልተኛ የምትላቸው የአማራ ልሂቃን አርበኞች ግንባር ብለው ቀድመው የተሰለፉት እነሱ ነበሩ፡፡ ዛሬም ያሉት እነሱው ናቸው--ንን ግድግዳ የሸበባ ዳስ ድርግላቸው እንጅ! እዚህ ላይ ራሴን ልቆጥብ…አናጋሪ አናግረኸኝ ነበር!

ከዚሁ ሳልወጣ ከራስህ ጋር መተራመስህን ለማሳየት ያህል ከቀናት በፊት በለጠፍከው ጽሁፍ እንዲህ ብለህ ነበር “እንግዲህ በደንብ እወቁት አማራ ነኝ። በእስክስታ ያደኩኝ፣ ጎራው ና የሚለውን እየዘመርኩ ከልጅነት ወደ ወጣትነት የገሰገስኩኝ። አዎ አማራ ነኝ፣ የምኮራበት ታሪክ እና ባህል ያለኝ፣ የጀግና አባቶች ልጅ። አማራ ነኝ፣ በጣልያን ቀንበር ስር ሲማቅቁ የነበሩ ባንዳዎችን ሳይቀር የታደኩኝ፣ በመቅደላ ላይ በአልበገርም ባይነት፣ ላገሬ በክብር የሞትኩኝ፣ አርሼ የምበላ፣ ፈትዬ ሸማ የምሰራ፣ የቅኔ ቤቱ ባላባት፣ የዜማ የድጎ መሰረት፣ የነ ዘራያቆብ ፣ የነ ዳዊት፣ የነ ሱስንዮስ፣ የነ ፋሲል፣ የነ ላሊበላ መፈጠሪያ ለኔም መፈጠሪያ የሆነ፣ አማራ ነኝ፣ እኔም መቅኒ መበጠስ፣ መሃል አገዳ መለየት አሳምሬ የማውቅ።” አንተ ነህ እዚህ ላይ በታሪክና ተረት ማኪቶህን የምትልፈው፡፡ ላንተ ሲሆን ታሪክ የጽሁፍ ማድመቂያ ነው፡፡ ለአማራ ልሂቃን ግን አሉባልታ ነው፡፡ እንዴት አይነት የተፋለሰ ሀሳብ እንዳለህ ታይበታለህ ብየ እገምታለሁ፡፡ ግን ይህ አይነት ሁኔታ የሚናገረውን አያውቅም ወይም ይዘላብዳል እድትባል ነው የሚያደርግህ፡፡

ልጅ ሄኖክ ቀጥለህል፡፡ አልከም “ትግሉን የሚጠሉት፣ ብርሃኑ እያደረገ ያለው ነገር ልክ አይደለም ብለው ስለሚያስቡ ሳይሆን፣ ገበናቸውን ስላጋለጠው ነው። ትግሉን የሚቃወሙት፣ እነሱ ማድረግ የማይችሉትን ነገር፣ ሌላ ሰው ሲያደርገው፣ በሰበካ ጉባዔ የገነቡትን ትልቅነታቸውን ስለሚንደው ነው።” በጣም የሚገርመኝ ብርሀኑ ትግል ማድረጉ የአማራ ልሂቃንን ገበና ማጋለጡ ነው፡፡ ኧረ ባባጃሌው! አሁንም የማይገናኝ ነገር፡፡ ለነገሩ ብርሀኑ እያደረገ ያለው ልክ አይደለም ቢሉህስ እንዴት ሊገባህ ይችላል! እኔ በትንሹ ልንገርህ ከገባህ፡፡ አንድ ቀን አንዱ “የወያኔና ሻዕብያ ተንኮል እንኳን ለሰው ለሰይጣን ስውር ነው” ብሎ ጽፎ አይቸው በጣም በዛ ሰው ማስተዋል ተገረምኩ፡፡ ወደዝርዝሩ አልገባም፤ ትግል አደናቃፊ ላለመባል፡፡ ግን አንድ የምነግርህ ነገር ይህ ነው፡፡ የኤርትራ ህዝብ እና የትግራይ ህዝብ እርስ በእርሱ ኩርፊያ ውስት እንጅ የምር ጥል ውስጥ አይደሉም፡፡ አንዱ ለአንዱ ጊዜያዊ ባላንጣ እንጅ ታሪካዊ ጠላት አይደለም፡፡ የሁለቱም ግን ከኩርፊያና ጊዜያዊ ባላንጣነት የዘለለ ታሪካዊ ጠላት አላቸው፡፡ እሱም አማራ ነው፡፡ ሻዕብያ በለው ኤርትራዊ (ፖለቲካዊ ትክክልነት ለጊዜው ይቆየን) አማራ ታሪካዊ ጠላቴ ነው ይላል፡፡ አርባ አመት ደም ተፍቶ የተዋጋውም አምርሮ ከሚጠላው አማራ ለመለየት ነበር፡፡ ይህ የታሪካዊ ጠላትነት አስረጅ ነው፡፡ ወያኔ እና የትግራይ ህዝብ አማራ ጣሪካዊ ጠላታችን ነው ይላሉ፡፡ ይህ በጥናት የተረጋገጠ እና በተግባርም እየታየ ያለ ነገር ነው፡፡ እዚህ ጋር ግን የምንነጋገረው ስለአብለጫው ቁጥረ መሆኑ ይሰመርበት፡፡ በዚህ የማይካተቱ አንዳንድ ሰዎች ስላሉ፡፡ ስለዚህ ሻእብያ የአማራ ልሂቃንንም ሆነ ታጋዮችን የሚስተናግዳው ከታሪካዊ ጠላትነት አንጻር እየመዘነ ነው፡፡ የከፋ ነገር ቢመጣ ሁለቱም ህዝቦችና ፓርቲዎች ከጋራ ታሪካዊ ጣታቸው አማራ ለመሸሽ ጊዜያዊ ባላንጣነታቸውን አቁመው አንድ መሆን የሚችሉ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ጦርነቱን የምታነሳ ከሆነ፤ ያ ጦርነት እንደኢትዮጵና ኤርትራ የተደረገ እንጅ እንደትግራይ ህዝብ እና እንደትግራይ ህዝብ አይደለም፡፡ ስለዚህ ከታሪካዊ ጠላት ጋር ከማበር ጊዜያዊ ጠላት ጋር ማበር ይቀላል፡፡ እናም የአማራ ልሂቃን ብለህ የምታብጠለጥላቸው ይህንን አጢነው በብስለት ወስነው ይሆናል ብሎ መገመትም ብልህነት ነው ልልህ ፈልጌ ነው፡፡ በተረፈ ያንተ “ክሽፈት እንደ አማራ ልሂቅነት ማለት ይህ ነው!” ተብሎ የተደመደመ ጠብደላዊ ዝብረቃ ሚዘኑ ቀሊል ነው፡፡ ምናልባት ይህ ያንተን ድፍረት ብቻ እንጅ እውነታውን አያመለክትም፡፡እኛም “ሄኖክ ዘባረቀ” እንጅ “ሄኖክ ተናገረ” በሚለው አንይዘውም፡፡

ልጅ ሄኖክ ከቀናት በፊት በለጠፍከው ጽሁፍ እንዶህ ብለህል “አማራ መሆን ያሳፍርም፣ አማራ ነኝ ማለትም አያሳፍርም። ይልቅስ እጅግ የሚያሳፍረው፣ አማራን ከሚያጠፉት ጋ ተሰልፎ ስለ ኢትዮጵያዊነት ማውራት፣ ወይስ አማራ እየጠፋ፣ እየተሰደደ፣ እየተገደለ፣ ለማይገባቸው ሰዎች ስለ አንድነት ልስበክ?” አወ፡፡ ምስኪን፡፡ ላንተ ሲሆን አማራ መሆን

አያሳፍርም፡፡ ለአማራ ልሂቃን ሲሆን ግን ተረትና አሉባልታ፤ ዘር ቆጠራ ይሆናል፡፡ እዚህ ልይ ድንቅ የሚለው ነገር አንድነት ለማይገባቸው ሰዎች አንድነትን መስበክ እንደማትፈልግ የገለጽክበት ነው፡፡ እንግዲህ ልብህን መርምር፡፡ ወረድ ብየ ገጽህን ሳየው በታሪክ የምናውቃቸውን ተቆጥሮ የማያልቁ የጀግኖች አማሮችን ፎቶ አስቀምጠሀል፤ ይሄ ነው አማራ ብሎ እንጉርጉሮ ቢጤ ያስቀመጥክበትም አለ፡፡ እዚህ ላይ ዋናው በነገብሪየና ገበየሁ ታሪክ እየተመጻደቀ የሚኖረው አንተ ነህ፡፡ እንደልመና ሽማ ዝናህን ለማዳመቅም ከሆነ የዘረጋሃቸው አላውቅልህም፡፡ ያው ከልብህ የማታደንቃቸውን አባቶች የንግድ ማሚሚቂያ አድርገሀቸዋል ማለት ነው፡፡ እንዲህም ብለህ አጠናከርከው "እንዲህ በዘር እና በጎሳ በሽታ የጦዘች ሀገር፣ እንዲህ በጥላቻ መርዝ የተለከፈች እና የተበከለች ሀገር፣ ስለ አንድነት መስበክ መጫወቻ መሆን የገባኝ ቆይቶ ነው።" ለአንባቢህ ግራ የሚሆነው በሶስት ቀን ውስጥ ከዚህ አቋም ተነስተህ 360 ዲግሪ ተሽከርክረህ መቆምህ ነው፡፡ ይህ ግን የጤና አይመስለኝም፡፡ ምን አነሳስቶህ ጸረ አንድነት አቋም እንዳንተባርቅክ እና ከሶስት ቀናት በኋላ ደግሞ ምን ነክቶህ እንደተገለበጥክ ተአምር ነው፡፡ በአንድ ሰው ላይ ይሄንን የመሰለ የተቃረነ ሰብእና ከተስተዋለ ሌላ ጥያቄ የሚስነሳ ነው፡፡

እናም እልሀለሁ፡- ወዳጀ የተማሩትን ለመተቸት እኮ መማር ያስፈልጋል፡፡ ገጣሚ ሁሉ ቋንቋና ብሂል አዋቂነትን እንጅ ልሂቅነትን አያመለክትም፡፡ ግጥሞች ትጽፋለህ…ጥንካሬያቸው ሌላ ነገር ሆኖ፡፡ ዞሮ ዞሮ ገጥም መጻፍ የተለየ እውቀትን አያመለክትም፤ የቋንቋ እና ብሂል ችሎታን እንጅ፡፡ እና በግሌ ልሂቃንን ለመተቸት የሚያስችል መሰረት አለህ ብየ አላምንም፡፡ ያው እደምታውቀው ፌስቡክ ሀሳዊ ልሂቅነት ካባ ደርቦልሀል እንጅ፡፡

ለግጥም ለግጥሙማ፡-

**እጸ በለስ ሆኖ ከንፈርሽ፤**

**መድኃኔ ዓለም ልቤ ተሰቀለልሽ፡፡**

ብሎ የሚገጥመው የአማራ ገበሬ ላንተ ግጥ ,ም ማስተማር ብቻ ሳይን አንተን ራስህን እንደገና ይፈጥርሀል፡፡ ያንተን የአመታት ስራ ብትጨምቀው የእነዚህን ሁለት ስንኞች ያህል ቁም ነገር ሊወጣው እንደማይችል አንተም ታውቀዋለህ፡፡ ያንተ አይነት ጠብደላዊ ድምዳሜ ካልሆነብኝ (ሀሀሀሀሀ)፡፡

በጣም የሚገርመው ቀደም ብለህ የጻፍካትን አማሮችን በበደኖና አርባጉጉ የገደላቸው ወያኔ እና ወያኔ ብቻ ነው ያልካትን አገላለጽ ባለ ብሩህ አእምሮዋ ሊድ ዘውዱ ከተቸችህ በኋላ ቆርህ አውጥተሀታል፡፡ ተመልሸሽ ስፈልጋት አጣኋት፡፡ ይህንን ያደረግከውም ከህግ አንጻር እንኳ የወንጀል አባሪ እና ተባባሪ ተብሎ ነው የሚቀጣው፤ ወንጀሉን ያቀናበረው እና ተልኮ የፈጸመው ምናልባት የቅጣት ሁኔታው ይለያይ እንደሁ እንጅ ሁለቱም ጥፋተኞች ከመሆን አይድኑም ተብለህ ስለተተቸህ ነው፡፡ ልጅ ሄኖክ ኦነግን ነጻ ስታወጣ ወይም ይህን ቀላል እውቀት አላወክም ወይም ለፖለቲካ ሽርሙጥና ስትል በሙታን አማሮች ስም ፖለቲካዊ ሸፍጥ እየሰራህ እንደሆነ ሲነገርህ ሽም ቆነጠጠህ መሰለኝ አጠፋሀት፡፡ የሚገርመው "ትግሬ እንዳይቀየም አማራ ይሙት" ብለህ ተችተህ የጻፍክ ሰው እዛው ላይ ኦነግን ነጻ በማውጣት ኦነግ እንዳይቀየም አማራ ይሙት አለይነት ነገር ጻፍክ፡፡

ልጅ ሄኖክ እንዴው የአማራ ምሁራንን በጅምላ ስትዘልፍ ጊዜ ምን ያህል የተራቀቀ ምሁር ነው ብየ ኢንተርኔት ላይ ስምህን አስገብቼ አሰስ አሰስ አደረግኩ፡፡ በስምህ የታተሙ ሳይንሳዊ ወረቀቶችን እና የኮንፈረንስ ጥናታዊ ስራዎችህን ባገኝ ብየ፡፡ አንዲትም ነገር ያላሳተመ ሰው ይህንን ሁሉ ስንት የሰራ ምሁር አንድ ላይ ጨፍልቆ ሊዘባበትበት አይችልማ! ይህንን

የመሰለ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አንተ ከሁሉም የበለጠ ስራ መስራት አለብህ፡፡ የፍሊጋየ ውጤት ግን ምንም ሆነ፡፡ ያገኘሁት ነገር ዩቱብ ላይ የተጫኑ "ግጥሞችህን" ነው፡፡ ረባም አልረባም እዚህ ላይ በርካታ ምስል አስቀምጠሀል ወይም ተቀምጦልሀል፡፡ ይህ ግን የአማራ ምሁራንን ልትተች ፈጽሞ አያስችልህም፡፡ አንድን ሳይንሳዊ ምርምር የሚደርግ ሰው በቧልት መሳይ ግጥም መተቸት አይቻልም፡፡ ምናልባ ብትተች የሚያምርብህ ከአቻነትም ከፍ የሚሉብህን እነ በውቀቱ ስዩም እና አበበ ቶላ መሰል ሰዎችን ነው፡፡ እነሱን ለመተቸትም አቅም የሚኖርህ አይመስለኝም፡፡ በጣም ያስከነዱሀል፡፡ እንዴ ከአንድም ሁለት ሶስት "መጽሀፍ" አሳትመዋል እኮ፡፡ አንተ አሳትመሀል እንዴ! እንደዛ ከሆነ ጥሩ፡፡

በተቃራኒው ዶክተር አበባ እና ዶክተር አሰፋ ነጋሽ (በውስጠ ታዋቂነት የዘለፍካቸው ለአማራ ተቆርቋሪ የሆኑትን እነሱን እና አቶ ተክሌ የሻውን መሰል ሰዎችን ነውና) አንብበኸው ለመረዳት እንኳ የሚከብድህን ጽነሰ ሀሳብ አፍልቀው ሰርተው ዘመናዊ ትምህርት የሚጠይቀውን ማእረግ ተጎናጽፈዋል፡፡ እውነት ለመናገር የእነዚህን ሰዎች ጫማ ለማሰር እንኳ ትበቃለህ ብየ አላምንም፡፡ በቪድየውም ከሄድክ ከአንተ ወላንሳየ ግጥሞች የዶክተር አሰፋ ነጋሽ እና አቶ ተክሌ የሻው ንግግሮች ወያኔን በተግባር ኢጋልጠዋል፤ ስፍር ቁጥር የሌለው አማራም አንቅተዋል፡፡ ዛሬ ለአማራነቱ የቆመው ወጣት የእነዚህ ሰዎች የስራ ውጤት ነው፡፡ "አማራ የለም" እያሉ የሚመጻደቁት አማርኛ ተናጋሪ አምላኮችህ አይደሉም ዛሬ የነደደውን የአማራ ብሔረተኝነት የለኮሱት፡፡ እውነቴን ነው እምልህ እነዚህን እና ሌሎች ምሁራንን ለመዝለፍ ምላስህን ከምታሞሙጥ ራስህን ብትፈትሽ ይሻልሀል፡፡

መለከ ሐራ ከቤተ አማራ